# ምስጢረ ትንሣኤ

## ጥያቄ፦ትንሣኤ ማለት ምን ማለት ነው?

ትንሣኤ ማለት መነሣት፣ መቆም ማለት ነው። ከበሽታ ድኖ መነሳት ትንሣኤ ነው። ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ ታሞና አልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን በሽተኛ (መፃጉዕ) ጌታችን ኢየስሱ ክርስቶስ፣ «ተነሳና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ» ባለው ጊዜ፣ በሽተኛው ሰው በጌታችን ቃል ከበሽታው ተፈውሶ አልጋውን ተሸክሞ ሄደ (ዮሐ.፭፥፱)።

በተለይም ከሞትና ከመቃብር በሕይወት መነሣት ትንሣኤ ይባላል። ሞቶ ከተቀበረ ከአራት ቀን በላይ የሆነውን አልዓዛርን ጌታችን በቃሉ፣ «አልዓዛር ሆይ፤ ተነሣ! ወደ ውጭ ና» ብሎ ከሞት አስነሣው፣ ከመቃብርአወጣው (ዮሐ.፲፩፥፵፫-፵፬)። ትንሣኤ ማለት ይህ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በተዋሐደው ሥጋ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ፣ በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱ  አማናዊ (እውነተኛው) ትንሣኤ ይባላል።

## ጥያቄ፦ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ማለት ምን ማለት ነው?

ሰዎች ከሞቱና ከተቀበሩ በኋላ፣ እንደገና ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር ሕይወትን አግኝተው ከሞትና ከመቃብር ይነሣሉ። ይህ ከሞትና ከመቃብር መነሣት፣ እጅግ ዐቢይና ድንቅ ነገር ስለሆነ፣የትንሣኤ ምስጢር ተብሎ ይጠራል።

## ጥያቄ፦ ምስጢረ ትንሣኤ በስንት ይከፈላል?

ምስጢረ ትንሣኤ በሁለት ይከፈላል። ይኸውም፦
ሀ. የጌታችን ትንሣኤ፣
ለ. የሰው ልጆች ትንሣኤ ነው።

## ጥያቄ፦የጌታችን ትንሣኤ እንዴት ነው?

ጌታችን በአዳም ምክንያት የመጣውን ሞት ይሽር ዘንድ በተዋሐደው ሥጋ ሞቶ ተቀበረ። ከዚያም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። የጌታችን መስቀልና ትንሣኤ ታሪክ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው።

ጌታችን ራሱ ስለ ሰው ልጆች ድኅነት በፈቃዱ መከራን እንደሚቀበል፣ በመስቀል እንደሚሰቀል፣ እንደሚሞትና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ አስቀድሞ፤ «እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፤ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል፤ የሞት ፍርድ ይፈርዱበታል፤ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል፤ ይዘቡቱበታል፤ ይተፉበታል፤ ይገርፉታል፤ ይገድሉታልም፤በሦስተኛውም ቀን ይነሳል» ሲል ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው (ማር.፲፥፴፬፤ ማቴ.፲፮፥፳፲-፳፪፤ ሉቃ.፲፰፥፴፩-፴፬፤ ማቴ.፳፥፲፯፲፱)። በዚሁ መሠረት፣ «ነቢያት ክርስቶስ ሰለ ሰው ልጆች መከራን ይቀበላል፤ ይሰቀላል፤ ይሞታል፤  በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ይነሳል» ብለው የተናገሩት ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ጌታችን መከራ መስቀልን ተቀበለ (ኢሳ.፶፫፥፩-፲፪፤ ዳን.፱፥፳፬-፳፯)።

# <u>የመስቀሉና የሞቱ ታሪክ</u>

<u>ጸሎት</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀልን ከመቀበሉ በፊት፣ ለእኛ አርአያ ለመሆን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለጸሎት ጌቴሴማኒ ወደምትባል ስፍራ ሄደ። ለደቀ መዛሙርቱም፣ «እኔ ወደዚያ ሄጄ እስክጸልይ ድረስ ከዚህ ቆዩ» አላቸው። ከዚያም ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ለመጸለይ ሄደ። እያዘነና እየተከዘ ለሦስቱ ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፣ እናንተ ከዚህ ቆዩ፣ ከእኔም ጋር ትጉ፤ ወደ ፈተናም እንዳትገቡ ጸልዩ» (ማቴ.፳፮፥፴፮-፴፰፤ ማር.፲፬፥፴፪-፴፭፤ ሉቃ.፳፪፥፴፱-፵፪)።

ጌታችን ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብና ከዮሐንስ የድንጋይ ውርውራ ያህል ርቆ ግንባሩ መሬት እያሰነካ በመስገድ፣ በተዋሐደው ሥጋ ወደ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አብ እንዲህ እያለ ጸለየ። «አባት ሆይ፤ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወደው ይሁን።» ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን፣ እንዲሁ ከእኔ ጋርአንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስ ተዘጋጅታለች፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው። ደግሞም ሁለተኛ ሄዶ እንዲህ እያለ ጸለየ፤ አባቴ ሆይ፤ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የሚቻል እንደሆነ ፈቃድህ ትሁን። ደግሞም ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው። ከዚያም ትቶአቸው ሄደ። ለሦስተኛም ጊዜ ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ። ከዚያ በኋላም ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ፣ እንግዲህስ ተኙ፤ዕረፉም፤ እነሆ ሰዓቲቱ ቀርባለች፤ የሰው ልጅም በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል። ተነሱ እንሂድ፤ እነሆ፤ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል» አላቸው። (ማቴ.፳፮፥፴፱-፵፮፤ ማር.፲፬፥፴፮-፵፪፤ ሉቃ.፳፪፥፵፪-፵፮)።

ጌታችን ይህንን ገና ሲናገራቸው ሳለ እንሆ፣ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፤ ከእርሱም ጋር ብዙ ሕዝብ ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከህዝቡ ሽማግሌዎች ዘንድ ወደ ኢየሱስ መጡ። አሳልፎ የሚሰጠውም፣ «እኔ የምስመው እርሱ ነውና ያዙት» ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር። ወዲያውም ወደ ኢየሱስ ቀረበና፣ መምህር ሆይ፤ ሰላም ላንተ ይሁን ብሎ ሳመው። ኢየሱስም «ወዳጄ ሆይ፤ ለምን ነገር መጣህ?» አለው። በዚህም ግዜ ቀረቡ፤ እጃቸውንም በኢየሱስ ላይ ጭነው ያዙት መጣህ?» አለው። በዚህም ግዜ ቀረቡ፤ እጃቸውንም በኢየሱስ ላይ ጭነው ያዙት(ማቴ.፳፮፡፵፯-፶፪፣ ማር.፲፬፤፵፫-፵፮፤ ሉቃ.፳፪፤፵፯-፶፫፤ ዮሐ.፲፰፤፩፩)።

**<u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን ሲጸልይ፣ «ይህች ጽዋ ...» ብሎ ያላት ምንድን ናት?**

ጌታችን በፈቃዱ በመስቀል ላይ ሊቀበላት የወደዳት ሞት፣ «ጽዋ» ብሎ ጠራት።

**<u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን፣ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑ የታወቀ ነዉ። እንደዚሁም ራሱ፦ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል» ብሎ ነበር። እንደዚሁም፣ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ፣ በጎቼ ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ ነጎቼ አሳልፌ እሰጣለሁ» ብሎ ስለ ስው ልጆች በፈቃዱ እንዲሞት አረጋግጦ ነበር (ዮሐ.፲፥፲፩-፲፮)። ታዲያ «ጽዋ» ብሎ የጠራውን ሞት እንዳያመጣበት ለምን ጸለየ?**

ጌታችን ስለ ዓለሙ ሁሉ ቤዛ ነፍሱን በፈቃዱ አሳልፎ እንደሚሰጥና እንደሚሞት፣ እንዲሁም ከሙታን ተለይቶ እንደሚነሣ አስቀድሞ ራሱ ተናግሮ እንደ ነበር የታወቀ ነው። የኸውም፣ «እኔ በፍቃዴ ነፍሴን አኖራታለሁ፤ ከእኔም ማንም አይወስዳትም፤ ላኖራት (አሳልፌ ልስጣት) ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሳት ሥልጣን አለኝ» ብሎ በተናገረው ቃል ይታወቃል (ዮሐ.፲፥፲፯-፲፰)።

ጌታችን የጸለየው ለአራት ነገር ነው፦

፩. ለአጽድቆተ ትስብእት ነው፤ ማለት ፍጹም ሰው መሆኑን ለማጠየቅ (ለማስረዳት)፤
፪. በመጸለዩ ለእኛ አርአያ ይሆነን ዘንድ፤
፫. ፍርሃተ ሞትን ከእኛ ለማስወገድ፤
፬. ለአቅርቦተ ሰይጣን፤ ማለት በፍርሃትና በትሕትና ሰይጣንን (ዲያብሎስን) ለማሸነፍነው።

ይህንን ታላቅ ምስጢር አስመልክቶ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደ ጌታችን ሆኖ የተናገረውን እንመልከት፤ «ዑቅ ርእሰከ ከመ አኮ በድንጋፄ ወበፈሪሃ ሞት ዘእቤ አባ እመ ይትከሃል ይኅልፍ እምኔየ ዝ፡ ጽዋዕ አላ በኅቡእ ቃለ ምስጢር በጥበብ ዘእብል አነ ዘንተ ስእለተ። ወዛቲ ቃል ምጽናሕት ይእቲ ለሰይጣን፤ እስመ ሐለወኒ በእላንቱ ቃላት አሥግሮ»፤ «አባት ሆይ፤ ቢቻል ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ብዬ የጸለይኩት በመደንገጥና ሞትን በመፍራት እንዳልሆነ አስተውል፤ ድንቅ በሆነ ምስጢር ይህን ጸሎት አደረስኩ እንጂ፤ ይህችም የጸሎት ቃል ለሰይጣን ወጥመድ ናት። በእነዚህም ቃላት ሰይጣንን ማጥመድ ይገባኛል» ሲል ተናግሮአል። ከዚያም ቀጥሎ እንዲህ ብሎአል፤ «ከመመሣግረ ጠቢብ ረሰይኩ ርእስየ፣ከመ ዘይፈርህ ወይደነግፅ እሞት፤ እቤ አባ እመ ይትከሀል ይኅልፍ እምኔየ ዝንቱ ጽዋዕ ከመ እምእላንቱ ቃላትየ ትሑታት ይመስሎ ከመስብእ ባሕቲቱ አነ ይጐጕዕ ወይተክል በማእከለ ምድር ዕጸ መስቀል»፤ «አባቴ፤ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ ብዬ በመጸለይ ሞትን እንደምደነግጥና እንደምፈራ እንደ ብልሃተኛ መሣሪያ (ወጥመድ) አደረግሁ። ከእነዚህ የፍርሃት ቃላት የተነሣ ሰይጣን እኔን ሰው ብቻ እንደሆንኩ መስሎት በምድር መካከል እኔ የምስቀልበትን ይተክል ዘንድ እንዲያፋጥን ብየ ነው» ብሎአል። (መጽሐፈ ግብረ ሕማማት፣ እትሙ ዘዓርብ፣ ገጽ ፪፻፶፱)።

በሌላም መንገድ፣ ከእኛ ፍርሃተ ሞትን ያስወግድ ዘንድ ጌታችን በለበሰው (በተዋሐደው) ሥጋ እንደ ፈራ የቤተክርስቲያን መምህራን አረጋግጠዋል። ለምሳሌ፣ ቅዱስ ሳዊሮስ ሊቀ ጳጳስ ዘአንጾኪያ እንዲህ ብሎአል፤ «ጌታችን ባይፈራስ ኖሮ ፍርሃት በሰው ላይ ለዘላለሙ ጸንቶ በኖረ ነበር፤ ባይታመምስ ኖሮ ሰዎች ከማዘን፣ ከመተከዝ ነፃ መሆንን ባላገኙም ነበር፤ ባያዝንም ኖሮ ኃዘናት ከእኛ ባልራቁም ነበር። ጌታችን ክርስቶስ እነዚህ ሕማማት (መከራዎች) በእርሱ ይፈጸሙ ዘንድ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በመታወካቸው ሥጋን በተዋሐደው በቃል ኃይል ጠፉ እንጂ»ሲል አስትምሮአል (ሳዊሮስ ሃይማኖተ አበው፣ገጽ ፫፻፷፰ ቍ.፲፬)።

## <u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን በጌቴሴማኒ ዐፀድ ጸሎቱን ከፈጸመ በኋላ ወዴት ሄደ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና፣ «ማንን ትፈልጋላችሁ?»አላቸው። እነርሱም፣ «የናዝሬቱን ኢየሱስን» ብለው መለሱለት። ኢየሱስም፣ «እኔ ነኝ» አላቸው። አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ከእርሱ ጋር ቆሞ ነበር። እንግዲህ፣ «እኔ ነኝ» ባላቸው ጊዜ፣ ወደ ኋላቸው አፈገፈጉ፤ በምድር ላይም ወደቁ። ደግሞም፣ «ማንን ትፈልጋላችሁ?» ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፣ «የናዝሬቱን ኢየሱስን» አሉት። ኢየሱስም መልሶ፣ «እኔ ነኝ አልኋችሁ እንግዲህ እኔን የምትፈልጉ ከሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተውአቸው» አላቸው (ዮሐ. ፲፰፥፮-፱)።

እንዲሁም ሊይዙት ለመጡት የካህናት አለቆች፣ ለመቅደስ አዛዦችና ለሕዝቡ ሽማግሌዎች እንዲህ አላቸው፣ «ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፈና ጎመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ስቀመጥ ሳለሁ አልያዛችሁኝም። ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነው የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ነው» ወዲያው የሻለቃው ጭፍሮችና የአይሁድም ሽማግሌዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት። አስቀድመውም ወደ ሐና ወሰዱት፤ በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ለነበረው ለቀያፋ አማቱ ነበረና (ዮሐ. ፲፰፥፲፪-፲፬)፤ ከዚያም ጻፎችና ሽማግሌዎች ወደ ተሰበሰቡበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት። (ማቴ. ፳፮፥፶፯)።

- የሐሰት ምስክሮች ተነሥተው በሐሰት እንዲመሰክሩበት አደረጉ (ማቴ. ፳፮፥ ፶፱-፷፫)፤
- በፊቱ ላይ ተፉበት፤
- ጐሰሙት፤
- «ክርስቶስ ሆይ፤ ራስህን የመታህ ማን ነው? በጥፊስ የመታህ ማን ነው?» እያሉ ራሱን መቱት፤ ፊቱን ሸፍነው ይጐስሙትና ትንቢት ተናገር ይሉት ነበር። ሌሎችም ፊቱን በጥፊ ይመቱት፣ በብዙም ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር (ማቴ. ፳፮፥፷፯፤ ማር.፲፬፥፷፭፤ ሉቃ.፳፪፥፷፫-፷፭)።

ከዚያም እንደ ታስረ ለመስፍኑ ለጴንጤናዊ ጲላጦስ አሳልፈው ስጡት (ማቴ.፳፯፥፩-፫)።

የገዢው የጲላጦስ ወታደሮች ኢየሱስን ያዙት፤ ጲላጦስም ኢየሱስን አስገረፈው። ወታደሮቹ ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ወሰዱት። ብዙ ጭፍሮች ወደ እርሱ አከማቹ። ልብሱን ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት፤ ከሾህም አክሊል ጐንጒነው በራሱ ላይ ደፋበት፤ በቀኝ እጁ ዘንግ አስያዙት፤ በፊቱም ተንበርክከው፤ «የአይሁድ ንጉስ ሆይ፤ ሰላም ላንተ ይሁን» እያሉ ዘበቱበት፤ ተፋበት፤ በዘንግ ራሱን መቱት። ከዘበቱበት በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፤ የራሱንም ልብስ አልብሰው ሊሰቅሉት ወሰዱት (ማቴ.፳፯፥፳፯-፴፪)።

ኢየሱስ መስቀል ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ(የራስ ቅል) ወደ ሚባለው ቦታ ደረሰ (ዮሃ.፲፱፥፲፯)። «ዋይ! ዋይ!» እያሉ የሚያለቅሱ ብዙ ሴቶችና ብዙም ሕዝብ ተከትለውት ነበር (ሉቃ.፳፫፥፳፯)። ወደ ቀራንዮም አውጥተው እየሱስን በዚያ ስቀሉት። ሁለት ክፉ አድራጊዎችንም አንዱን በግራው አንዱን በቀኙ ከእርሱ ጋር ሰቀሉ (ሉቃ.፳፫፥፴፪-፴፫)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲሄድ ከግርፋቱ፣ ከብትሩና ከጥፊው ብዛት የተነሣ በመንገድ እየወደቀና እየተነሳ ይጓዝ ነበር። ወታደሮቹም ያዳፉትና ያጣድፉት ነበር። ከድካሙ ብዛት የተነሣ እንደ ጣማው አይተው፣ በሐሞት የተደባለቀ መራራ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ አቀረቡለት፤ እርሱም ሊጠጣ ስለልፈለገ ቀምሶ ተወው (ማቴ.፳፯፥፴፬)።

ኢየሱስን ከሰቀሉት በኋላ ልብሱን ዕጣ ተጣጥለው ተካፈሉት (ማቴ.፳፯፥፴፭-፴፯)። ኢየሱስም፣ «አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር በላቸው» ብሎ ጸለየላቸው (ሉቃ.፳፫፥፴፬)። ከዚያም የመጸሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ፣ «ተጠማሁ» አለ። በዚያም ኢየሱስ ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፣ «ተፈጸመ» አለ፣ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አስልፎ ስጠ (ዮሐ.፲፱፥፳፰-፴)።

ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በሥልጣኑ ለየ። በዚህ ጊዜ፣ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ፣ በሲኦል ተይዘው የነበሩትን ነፈሳት አወጣ፤ ዘላለማዊ ሕይወትንም ስጣቸው።

ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ያስተማረውን እንመልከት፤ «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር አብ ያቀርበን ዘንድ እርሱ ኃጢአት የሌለበት ጻድቅ ነው፤ እርሱም ሄዶ በወህኒ (በሲኦል) ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው» ብሎአል (፩ጴጥ.፫፥፲፰-፳)።

ጌታችን በተዋሐደው ሥጋ በፈቃዱ ከሞተ በኋላ ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ከጌታ ጐን ደምና ውኃ ወጣ (ዮሃ.፲፱፥፴፬-፴፭)። ከዚህም የተነሣ በውኃው እንጠመቅበታለን፤ ደሙንም በቊርባን ጊዜ እንቀበለዋለን።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድና በሮማውያን ወታደሮች ተይዞ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ በመስቀል ከተሰቀለበትና በፈቃዱ ሞትን እስከ ቀመሰበት ድረስ ሰለ እኛ የተቀበለው መከራ እጅግ ብዙ ነው፤ የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ግን ጌታችን ከተቀበላቸው መከራዎችመካከል ዋና ዋናዎቹን አሥራ ሦስት ብለው ቆጥረዋቸዋል።

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፦

1. ተአስሮ ድኅሪት - እጆቹን የኋሊት መታሰሩ፣
2. ተቀሥፎተ ዘባን - ጀርባውን መገረፉ፣
3. ወሪቀ ምራቅ - በላዩ ላይ ምራቃቸውን መትፋታቸው፣
4. ተኰርዖ ርእስ - ራሱን በብትር መመታቱ፣
5. ተጸፍዖ መልታሕት - ፊቱን በጥፊ መመታቱ፣
6. ጸዊረ መስቀል - መስቀሉን መሸከሙ፣
7. አክሊለ ሦክ - የሾክ አክሊል መቀዳጀቱ፣
8. ስትየ ሐሞት - ሃሞት መጠጣቱ፣
9. ተቀንዎተ እእዳው - በሁለት ችንካር እጆቹን መቸንከሩ፣
10. ተቀንዎተ እግር - በሁለት ችንካር እግሮቹን መቸንከሩ።

ጌታችን የተቀበላቸው መከራዎች ፣ ከሁለቱ የእጆቹን ችንካሮች ጋር አሥር ይሆናሉ። እንደ ገና ሁለቱ የእግሮቹ ቅንዋት ሲደመሩ አሥራ ሁለት ይሆናሉ። ርግዘተ ገቦ፣ ጎኑን በጦር የወጉት ሲጨመርበት አሥራ ሦስት ይሆናሉ። ስለዚህ ሊቃውንት እነዚህን «አሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል» ይሉአቸዋል።

**ጥያቄ፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰለ እኛ ኃጢአት፣ ስለ እኛ በደል በተስቀለ ጊዜና ስለተዋሐደው *ሥጋ* በፈቃዱ ሞትን በቀመሰ ጊዜ የተፈጸሙ ታላላቅ ተአምራት ስንት ናቸው?**

ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ከተፈጸሙት ታላላቅ ተአምራት መካከል ዋና ዋናዎቹ ሰባት ናቸው። እነርሱም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩. ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ጨለማ ሆነ (ማቴ.፳፯፥፵፭)፤
፪. ፀሐይ ጨለመች (ሉቃ.፳፫፥፵፭)፤
፫. በኢየሩሳሌም የነበረው በቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ (ማር.፲፭፥፴፰)፤
፬. ምድር ተናወጠች (ተንቀጠቀጠች)፤
፭. አለቶች ተሰነጠቁ፤
፮. መቃብራት ተከፈቱ፤
፯. በመቃብር ተቀብረው የነበሩ ብዙ ሙታን ተነሡ፤ ከጌታችን ትንሣኤ በኋላም ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎቹ ታዩ (ማቴ.፳፯፥፶፩-፶፬)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ በደል መከራ መስቀልን በተቀለበት፣ በተዋሐደውም *ሥጋ* ሞትን በቀመሰበት ወቅት፣ እጅግ በርከት ያሉ ከገሊላና ከእየሩሳሌም የተከተሉት ቅዱሳት አንስት በቀራንዮ ተገኝተው በታላቅ ኀዘን ተውጠው የሚቀበለውን መከራ ሁሉ በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር። ከእነርሱም መካከል መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም፣ የዘብዴዎስ ልጆች የዮሐንስና የያዕቆብ እናት ማርያም፣ ሰሎሜና ሌሎችም ነበሩ (ማቴ.፳፯፥፶፭-፶፮ ፤ ማር.፲፭፥፵፩፤ ሉቃ.፳፫፥፵፱)። ከእነርሱም ጋር የጌታችን እናት ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም፣ እኅቷ ሰሎሜ፣ የቀለዮጳ ሚስት ማርያምና ሌሎች ብዙ ቅድሳት ሴቶች ነበሩ (ዮሐ.፲፱፥፳፭)።

**ጥያቄ፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ስለሆነ በሰውነቱ ሞትን ቀምሶ ቅድስት ነፍሱን ከቅድስት *ሥጋው* ከለየ በኋላ ቅዱስ *ሥጋው* የት ተቀበረ? እነማንስ ቀበሩት?**

*የጌታችን ቅዱስ ሥጋ የተቀበረው፣ ጌታችን በተሰቀለበት አካባቢ በነበረው ዐፀድ ውስጥ ነው። የቀበሩትም የጌታችን ደቀ መዛሙርት የሆኑ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ናቸው። የመቃብሩም ታሪክ እንደሚከተለው ነው፡-*

ጌታችን በተሰቀለበት በዕለተ ዓርብ ምሽት ላይ ዮሴፍ የተባለው የአርማትያስ ሰው ወደ ቀራንዮ መጣ። ይህ ሰው የጌታችን ደቀ መዝሙር ነበር። እርሱም ባለጠጋና አይሁድ የሸንጎ አማካሪዎች አንዱ ከመሆኑም በላይ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት መምጣት የሚጠባበቅ ጻድቅ ሰው ነበር። ይህ ሰው ደፍሮ ወደ ጲላጦስ ገብቶ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የነበረውን የኢየሱስን *ሥጋ* አውርዶ ለመቅበር እንዲፈቅድለት ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። በዚህ ጊዜ ዮሴፍ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ *ሥጋ* ከመስቀል አውርዶ በንጹሕ በፍታ ከፈነው። ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ክርስቶስ መጥቶ የነበረው ኒቆዲሞስ፣ መቶ ንጥር የሚያህል እጅግ የከበረ ሽቱ ይዞ መጣ። ዮሴፍና ኒቆዲሞስም ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አይሁድ የአገናነዝ ልማድ ከከበረ ሽቱ ጋር በንጹሕ በፍታ (በተልባ እግር ልብስ) ከከፈኑት በኋላ ጌታችን በተሰቀለበት አጠገብ ከዓለት ከተቀበረ፣ ከዚያ በፊት ማንም ሰው ባልተቀበረበት አዲስ መቃብር አኖሩት (ቀበሩት)፤ መቃብሩንም በታላቅ ድንጋይ ዘግተውት ሄዱ።
ከገሊላም ጌታችንን ተከትለው የመጡ ማርያም መግደላዊት፣ የዮሳና የያዕቆብ እናት ማርያምና ሌሎቹ ጌታችንን የት እንደ ቀበሩት አይተውና ተመልክተው ወደ ስፈራቸው ተመለሱ (ማቴ.፳፯፥፶፯-፷፩፤ ማር.፲፭፥፵፪-፵፯፤ ሉቃ.፳፫፥፶-፶፮፤ዮሐ.፲፱፥፴፰-፵፪)።

የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ከመቃብር ይነሣል ብለው ስለ ሠጉ፣ ወደ ጲላጦስ ሄደው፣ «ጌታ ሆይ፤ ያ ሰው ገና በሕይወቱ ሳለ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ ማለቱ ትዝ አለን። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት ሄደው እንዳይሰርቁትና ለሕዝቡም ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ፣ የኋለኛይቱም ስሕተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች እንዳትሆን፣ መቃብሩ እስከሦስት ቀንድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት። ጲላጦስም፣ «ጠባቆች አሉአችሁ

እንዳወቃችሁ አስጠብቁ» ብሎ መለስላቸው። ነቅተው፣ ተግተው፣ እስከ ሦስት ቀን ይጠብቁ ዘ ንድ ወታደሮች አዘዘላቸው።
እነርሱም ሄድው ከጠባቆቹ ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ (ማቴ.፳፯፥፷፬-፷፮)።
በዚህ ዓይነት ጌታችን ከመቃብር እንዳይነሣ በመፍራት፣ ሊቃነ ካህናቱና ፈሪሳውያን ጌታችን የተቀበረበትን መቃብር ወታደሮቹ ነቅተው፣ ተግተው እስከ ሦስት ቀን እንዲጠብቁ አደረጉ። መ ቃብሩ  የተዘጋበት ታላቅ ድንጋይም እንዳይለወጥ በመሥጋት በማኅተማቸው አተሙበት።
ሕይወትን የሚያድል የሕያዋን አምላክ ክርስቶስ በለበሰው *ሥጋ* (በተዋሐደው *ሥጋ*) ሞቶ፣ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በመቃብር ተቀብሮ ቆየ። ስለ እኛ ሞትን ቀምሶ በመቃብር ሦስት ቀን ና ሦስት ሌሊት ተቀብሮ እንደሚቆይ እርሱ ራሱ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ይኸውም በሞትና በመቃብር ሥልጣን ሥር ለነበሩት ሁሉ የሕይወት የድኅንነት ምልክት ይሆን ዘንድ ነው።
ጌታችን ወንጌለ መንግሥትን እየሰበከና የማዳን ሥራውን እየፈጸመ በየቦታው በሚዘዋወርበት ወቅት፣ ከጻፎችና ከፈሪሳዊያን አንዳንዶቹ፣ «ጌታችን መምህር ሆይ፣ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን» አሉት። እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፣ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፤ ከነቢዩ ከዩናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በምድር ልብ (በምድር ውስጥ) ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል» ብሎ የነገራቸው ቃል ተፈጸመ (ማቴ.፲፪፥፴፰-፵፩)።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ስለሆነ፣ በሰውነቱ ማለት በተዋሐደው *ሥጋ* ሞትን በቀመስ ጊዜ ቅዱስ *ሥጋ*ውን ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በንጽሕ በፍታ ገንዘው በመቃብር ሲያኖሩት፣ ለመለኮቱ በሰማይና በምድር ምሉዕ ሆኖ የሚገኝ አምላክ ነው። መለኮት የተዋሐደ ው ቅዱስ *ሥጋ*ው ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በመቃብር ሳለ፣ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚ ያ የነበሩትን ነፍሳት ነጻ አወጣ። ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በ*ሥጋ*ው በመቃብር ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት ሳለ በመለኮቱ ፍጹም ነውና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከአምላካዊ መንበሩ አ ልተለየም። ይህን በሚመለከት በአራተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበ ረው ቅዱስ ፕሮክልዮስ (ኤራቅሊስ) ያስተማረውን ትምህርት እንመልከት፤ «ጌታዬ ፈጣሪዬ አን ተ ነህ፤ ቅድመ ዓለም የነበርክ አንተ ነህ፤ ዛሬም ያለህ አንተ ነህ፤ ሰማያዊ አንተ ነህ፤ ምድራዊ ም አንተ ነህ፤ በሰማይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህልው የምትሆን አንተ ነህ፤ ዓለም ሳይፈ ጠር ጀምሮ በአምላካዊ መንበርህ ያለህ አንተ ነህ፤ አሁንም በዕፀ መስቀል ላይ የተቸነከርክ አን ተ ነህ፤ በ*ሥጋ* መከራን የተቀበልክ አንተ ነህ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ እንደ መሆንህ ሞት የሌለብህ አንተ ነህ፤ ከእኛ ጋር አንድ እንደ መሆንህ በፈቃድህ የሞትህ አንተ ነህ፤ በመቃ ብር ያደርህ አንተ ነህ፤ በኪሩቤል ላይ ያለህ አንተ ነህ፤ ከሙታን ጋር በመቃብር ያደርክ አንተ ነህ፤ ባንተ ሕማምና ሞት ድኅነት ተሰጠ። ከሙታን ጋር የተቆጠርክ አንተ ነህ፤ ለሙታን ትንሣ ኤ የምትሰጥ አንተ ነህ፤ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በመቃብር ያደርህ አንተ ነህ፤ በመለኮት ህ ሕማም ሳይኖርብህ በ*ሥጋ* የታመምህ አካላዊ ቃል አንተ ነህ (ሃይማኖተ አበው ገጽ 150)።

## ትንሣኤ ክርስቶስ (የክርስቶስ  ትንሣኤ)

**ጥያቄ፦ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው መቼ ነው ?**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሐደው *ሥጋ* ከሞተና ከተቀበረ በኋላ በሦስተኛው ቀን እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፡፡

**ጥያቄ፦ጌታችን በማን ሥልጣንና በማን ኃይል ተነሣ ?**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ሥልጣንና በራሱ ኃይል ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፡፡ ጌታችን በፈቃዱ ስለ እኛ ለመሞትና በሥልጣኑም ከሙታን ተለይቶ ለመነሣት ሙሉ ሥልጣን እንዳለው አስቀድሞ፤ «ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ»

**ጥያቄ፦ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው በራሱ ኃይልና በራሱ ሥ ልጣን ከሆነ ሐዋርያት በተለይም ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ጳውሎስ፤ «እግዚአብ**

## ሔር ከሙታን አስነሣው» ብለው ለምን አስተማሩ? (የሐዋ. ፫፥፲፭፤፬፥፲፤፭፥ ፴፩፤ ሮሜ ፰፥፲፩፥፲፥፱)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋንና ለባዊት ነፍስን ተዋሕዶ ከኃጢአት በቀር ፍጹም ሰው ከመሆኑ በፊት «ወልደ እግዚአብሔር፤ ቃለ እግዚአብሔር፤ አምለክ ወልድ አምላክ» እየተባለ ይጠራ ነበር እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ አይጠራም ነበር። ከኃጢአት በቀር ያለመለዋወጥ ፍጹም ሰው ከሆነ ወዲህ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ተጠራ። በሰውነቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወለደችው፤ ሰው በመሆኑ ማለት በሰውነቱ (በተዋሐደው ሥጋ) በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ፤ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ (ማቴ.፫፥፲፫፤ ፬፥፩-፲፩) በተዋሐደው ሥጋ ጸለየ (ማቴ. ፳፯፥፵፮-፶፮)። ፍጹም ሰው መሆኑን ለማስረዳትም ከኃጢአት በቀር ሰው የሚሰራውን ሥራ ሁሉ ሠራ። በሰውነቱ መከራ መስቀልን ተቀብሎ ሞትን ያጠፋ ዘንድ ሞተ (ዮሐ. ፲፱፥፴) ስለዚህ ቅዱሳን ሐዋርያት እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው ብለው ማስተማራቸው ክርስቶስ በመለኮቱ ኃይል መነሣቱን ለማረጋገጥ ነው። ምክንያቱም ሰው በመሆኑ ኢየሱስ ተብሎ የተጠራው ወልደ እግዚአብሔር በመለኮት ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ (ትክክል) ነውና፤ በባሕርዩም እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነውና፤ በዚሁ መሠረት «እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው» ማለት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የቀበሩትን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር በመለኮቱ ኃይል ማስነሣቱን ለማረጋገጥ ነው። ይኸውም ክርስቶስ በተዋሐደው ሥጋ ሞቶ በመለኮቱ ሕያው ሆኖ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ያመለክታል፤ መለኮት የተዋሐደው የክርስቶስ ሥጋም በመለኮት ኃይል መነሣቱን ያረጋግጣል። ክርስቶስ በመለኮቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኮል (ትክክል) እንደሆነ፤ ማለት አንድ መሆኑን ራሱ ሲያረጋግጥ «እኔና አብ አንድ ነን» ብሎአል (ዮሐ.፲፥፴)። የአብ ሥልጣን የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን እንደሆነ ለአብ ያለው ሁሉ የወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ እንደሆነ ሲያረጋግጥ «ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው» ብሎአል (ዮሐ.፲፮፥፲፭)።

ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ በገዛ ሥልጣኑ (በመለኮቱ) ሥጋውን ከመቃብር እንደሚያስነሣ ራሱ አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። ይኸውም «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት እኔም በሦስት ቀን አነሣዋለሁ» ብሎ ለአይሁድ መናገሩ ታውቋል (ዮሐ.፪፥፲፱-፳፪)።

ይህንን ምስጢር ተከትለው ብዙ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አስፍተው ጽፈዋል። ለምሳሌ ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ የጻፈውን ከዚህ ቀጥለን እንመልከት፤ «እኛም እግዚአብሔር አብ ከእርሱ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእም ባሕርይ የተወለደው ወልድ በባሕርዩ ሕይወት እንደሆነ እንናገራለን፤ በዚህ አነጋገር አብ ክርስቶስን አስነሣው ተብሎ ቢነገርም፤ እኛ እራሱ ራሱ ወልድ ራሱን እንደ አስነሣ የሚናገር እናገኛለን እርሱ አይሁድን «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት እኔም በሦስተኛው ቀን አነሣዋለሁ» ብሎአቸዋል (ሃይማኖተ አበው፤ ገጽ ፫፻፴፫ ቁ.፮)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገና መከራ መስቀልን ከመቀበሉ በፊት ሞትን አሸንፎ ከሙታን ተለይቶ በራሱ ሥልጣን እንደሚነሣ በማረጋገጥ፤ «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት እኔም በሦስተኛው ቀን አነሣዋለሁ» ባላቸው ጊዜ አይሁድ «ይህ ቤተ መቅደስ በአርባ ስድስት ዓመት የታነጸ ሲሆን አንተ በሦስት ቀን ታአነሣዋለህን?» ሲሉ መለሱለት። አይሁድ ይህንን ያሉበት ምክንያት ኢየሱስ የተናገረው ስለ ቤተ መቅደሱ መስሎአቸው ነበር፤ ኢየሱስ ግን እንዲህ ብሎ የተናገረው ስለ ራሱ ሥጋ( ስለ ራሱ ሰውነት) ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚያ ብሎ የተናገረው ስለ ራሱ ሰውነት (ስለ ሥጋው) እንደሆነ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ተረዱ፤ ጌታችን በራሱ ሥልጣን ሥጋውን እንዳስነሣም አመኑ (ዮሐ.፪፥፳-፳፪)።

## <u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ያበሠሩ እነማን ናቸው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ለመጀመሪያ ጊዜ ለሰው ልጆች ያበሰሩ ቅዱሳን መላእክት ናቸው። ታሪኩም እንደዚህ ነው፦

ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም የጌታን መቃብር ሊያዩ ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው እጅግ ማልደው ወደ መቃብሩ መጡ። እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ፤ መልኩ እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረድ ነጭ ነበር፤ ጠባቆቹም (መቃብሩን የሚጠብቁ) መልአኩን ከመፍራት የተነሣ ተንቀጠቀጡ እንደ ሞተም ሆኑ። መልአኩም ሴቶቹን፦ «እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን

እንድትሹ አውቃለሁና፤ እንደ ተናገረው ተነሥቶአልና፤ በዚህም የለም የተኛበትን ሰፍራ (ተኝቶበት የነበረውን ሰፍራ) ኑና እዩ፡፡ ፈጥናችሁም ሂዱና ከሙታን ተነሣ እነሆም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው፤ እነሆም ነገርኋችሁ አላቸው» (ማቴ.፳፰፥፩-፯)

ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው ወንጌል መሠረት ደግሞ የጌታ ትንሣኤ ታሪክ በአጭሩ እንዲህ ነው፤ «ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው እጅግ ማልደው ወደ መቃብሩ መጡ፡፡ ድንጋዩም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም፤ እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ እነሆ ሁለት ሰዎች (መላእክት) የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ ሴቶቹም ፈርተው ወደ ምድር አቀርቅረው ሳለ እንዲህ አሉአቸው፤ ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም የሰው ልጅ በኃጢያተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ይገባዋል እያለ በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ አስቡ፡፡ ከመቃብር ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለሌሎቹ ሁሉ ነገሩአቸው» (ሉቃ.፳፬፥፩-፲)፡፡ እንደዚሁም በማርቆስ ፲፮፥፩-፲፩ በዮሐ.፳፥፩-፲፰ በተመሳሳይ ሁኔታ ታሪኩ ተመዝግቦአል፡፡

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለእነ ማን ተገለጠላቸው?

ጌታችን ሞትን አሸንፎ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በመጀመሪያ ለማርያም መግደላዊት ተገለጸላት (ዮሐ.፳፥፩-፲፰)፡፡ ከዚያም ለማርያም መግደላዊትና ለሌሎች ቅዱሳት ሴቶች በመንገድ ተገለጸላቸው (ማቴ.፳፰፥፱)፡፡ እንደዚሁም ወደ ኤመሁስ ሲሄዱ ለነበሩት ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት ተገለጸላቸው (ሉቃ.፳፬፥፲፫-፴፭)፡፡ ቀጥሎም ወደ ገሊላ ተራራ ሄደው ይጠብቁት ለነበሩት ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ተገለጠላቸው (ማቴ.፳፰፥፲፮)፡፡ በተጨማሪም በተዘጋ ቤት ተሰብስበው ለነበሩት ለአሥሩ ደቀ መዛሙርት ተገልጦና በመካከላቸው ቆሞ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው፡፡ ይህንንም ብሎ እጆቹንም፤ ጎኑንም አሳያቸው ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው (ዮሐ.፳፥፲፱-፳)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለእነማን እንደ ተገለጸ ሲመሰክር «መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም፤ መጽሐፍ እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ፤ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፡፡ ከእነርሱም የሚበዙት እስከ አሁን አሉ፤ አንዳንዶቹ ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ በኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ፤ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ» ሲል አስረድቶአል (፩ቆሮ.፲፭፥፫-፱)

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞት ላይ አሸናፊ ሥልጣን እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለ ወይ?

አዎን አለ፤

፩ኛ. የአንድ መኮንን ልጅ ከሞተች በኋላ ጌታችን እጅዋን ይዞ ከሞት አስነሥቶአታል (ማቴ.፱፥፲፰-፳፮)፤

፪ኛ. የአንዲት መበለት ልጅ ሞቶ ሊቀብሩት በቃሬዛ ይዘው ወደ መቃብር ሲወስዱት በድንገት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀርቦ ቃሬዛውን ነካ፤ ቃሬዛውን የተሸከሙትም ቆሙ፤ በዚያን ጊዜ ጌታችን፤«አንተ ጎበዝ ተነሥ እልሃለሁ» አለው የሞተውም ሰው ወዲያው ቀና ብሎና ተነሥቶ ተቀመጠ (ሉቃ.፯፥፲፩-፲፮)፤

፫ኛ. ሞቶ ከተቀበረ አራት ቀን የሆነውን አልዓዛርን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መቃብሩ ሄዶ ከመቃብሩ ፊት ለፊት በመቆም «አልዓዛር! አልዓዛር! ፤ ተነሣ ወደ ውጭ ውጣ!» ብሎ ጠርቶ ከሞት አስነሥቶታል (ዮሐ.፲፩፥፲፯-፵፬)፡፡

በዚሁ መሠረት ሞት በጌታችን ላይ ሥልጣን ሳይኖረው ጌታ ግን በሞት ላይ ሙሉ ሥልጣን ስላለው ከሞት ለማስነሣት የፈለጋቸውን ወዳጆቹን ከሞት በማስነሣቱ፤ በሞት ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው መሆኑ ተረጋግጦአል (ዮሐ.፭፥፳፩)፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሕይወትና

ትንሣኤ ነውና (ዮሐ.፲፩፥፳፭-፳፮)፡፡ እንደገናም ራሱ ሞትን አሸንፎ ከሙታን ተለይቶ ከተነሳ በኋላ ፤ «ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ፤ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረ ስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ» ብሎአል (ራዕ.፩፥፲፯-፲፰)፡፡ በዚህኛው ቃል ጌታ ችን በሞትና በሲኦል ላይ ሙሉ ሥልጣን እነዳለው ተረጋግጦአል፡፡ ይህም ማለት ጌታችን ሞትንና ሲኦልን ማዘዝ፤ መሰር፤ ማስወገድና መጥፋት የሚችል ኃያል አምላክ ነው ማለት ነው፡፡

ሞትና ሲኦል በጌታችን አምላካዊ ሥልጣን ድል መሆናቸውን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ □ ጳውሎስ ሲመሰክር «ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ (ኦሪት)ነው፤ ነገር ግን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣቱን ለሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» ብሎአል (፩ቆሮ.፲፭፥፶፭-፶፮)

## <u>ጥያቄ</u>፡- በሞትና በሲኦል ላይ የአሸናፊነት ሥልጣን ያለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ን ድል አድርጎና ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ ለእኛ ለሰው ልጆች የሰጠን ጥቅም ምንድር ነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሣኤው የሰጠን ታላቅ ጥቅም ከሞት በኋላ ሕይወትንና ትንሣኤን መግኘት ነው፡፡ ይኸውም እርሱ ራሱ «ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለ ውከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» ብሎ ከሞት የመነሣትና የዘላለማዊ ሕይወትን የመውረስ መብት ሰጥቶናል ዮሐ.፭፥፳፬)፡፡

በተለይም ጌታችን ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ ከሞትና ከመቃብር መነሣት ለሚገባቸው የሰው ልጆች በሙሉ በኩር ሆኖአል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከመቃብር ለሚነሡ ሁሉ ጀማሪ በኩ ር መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ «አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀለፋት ሁሉ በኩር ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል ሞት በሰው በኩል መጣ፤ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል (በክርስቶስ በኩል) ሆኖአል፡፡ ሁሉ ባዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ» ብሎአል (፩ቆሮ.፲፭፥፳-፳፪)

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ከሙታን አልተነሣም ብለው ለማስተባበል ሲሉ በጌታ መቃብር ዙሪያ ነቅተ ው ተግተው ይጠብቁ የነበሩት ወታደሮች ጌታችን በታላቅ ሥልጣን ከሙታን ተለ ይቶ በተነሣ ጊዜ ምን ሆኑ?

ጌታችን ተቀብሮበት በነበረው ቦታ የእግዚአብሔር መልአክ ስለ ወረደበት እጅግ ተናወጠች (ተንቀጠቀጠች)፡፡ ከሰማይ የወረደውም መልአክ እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረድ ነጭ ነበር ጠባቆችም መልአኩን ከመፍራት የተነሣ ተንቀጠቀጡ እንደ ሞቱም ሆኑ ይላል ((ማቴ.፳፰፥፪-፬) ስለዚህ ነቅተው ተግተው ይጠብቁ የነበሩት ወታደሮች መልአኩን አይተው በመደንገጥ ወደቁ እንደ ሞቱም ሆኑ፡፡

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ወዴት ሄደ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን አሸንፎ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በኢየሩሳሌም በገሊላ ተራራና በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጸ ምስጢረ ትንሣኤውን ሲያስተምራ ቸውከቆየ በኋላ ከሙታን በተነሣ በአርባኛው ቀን በታላቅ ክብርና በምስጋና ወደ መጣበት ወደ ሰማ ይ ወደ ላከው ወደ አብ ዐረገ (የሐዋ.፩፥፩-፲፩)፡፡

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ክብርና በምስጋና ወደ ሰማይ ከማረጉ (ከመውጣቱ) በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ምን አላቸው?

መልስ፡-

፩ኛ. አርባ ቀን ሙሉ እየታያቸው ማለትም እየተገለጸላቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እያስተማራቸው ከሕማሙ በኋላ ሕያው መሆኑን በብዙ ማስረጃ ራሱን ገለጸላቸው፤

፪ኛ. «እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ» ብሎ አዘዛቸው(ሉቃ.፳፬፥፵፰-፵፱)፡፡

፫ኛ. «ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን ተሰፋ ቃል ጠብቁ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» አላቸው (የሐዋ.፩፥፬-፭)፡፡

፬ኛ. «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምና በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እሰከ ምድርም ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሁናላችሁ» አላቸው(የሐዋ.፩፥፰-፱)፡፡

ከዚህ በኋላ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን እስከ ቢታንያ አወጣቸው፤ እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ፡ እነርሱም ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በመቅደስ ኖሩ (ሉቃ.፳፬፥፶-፶፫)፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በአርባኛው ቀን በታላቅ ክብርና በብዙ ምስጋና ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ አንገታቸውን ወደ ሰማይ አቅንተው ወደ ሰማይ በማረግ (በመውጣት)ላይ የነበረውን ጌታችንን ትኩር ብለው ሲመለከቱ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች (መላእክት) ባጠገባቸው ቆመው እንዲህ አሉአቸው «እናንት የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን እዚህ ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል (ይመለሳል) (የሐዋ.፩፥፲-፲፩)፡፡

ጌታችን ወደ ሰማይ ባረገ በአሥረኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ በአምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት ላከላቸው፤ ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ተቀበሉ በልዩ ልዩ ቋንቋም ተናገሩ (የሐዋ.፪፥፩-፬)፡፡

## <u>ዳግም ምጽአተ እግዚእነ (የጌታችን ዳግመኛ መምጣት)</u>

### <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክብርና ምስጋና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ አንደገን ወደዚህ ዓለም ተመልሶ ይመጣልን?

አዎን ወደዚህ ዓለም ተመልሶ ይመጣል፡፡ ጌታችን ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደሚመጣ ራሱ መድኃኒታችን ወደ ሰማይ ባረገበት ወቅት ባጠገቡ ቆመው የነበሩት መላእክት «እናንት የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል» ብለው በዚያ ቆመው ለነበሩት ለቅዱሳን ሐዋርያት አረጋግጠውላቸዋል (የሐዋ.፩፥፲-፲፩)፡፡□

### ጥያቄ፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ቀደም ብሎ የተነገረ ትንቢት አለ ወይ?

አዎን አለ፤ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ይገኛል፡፡ ከዚህ ቀጥለው ያሉት ጥቅሶች ከቡዙ ጥቂቶቹ ናቸው፤

፩ኛ. «እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ (በግልጥ)ይመጣል፤ አምላካችን ይመጣል (ይመለሳል)፤ ዝምም አይልም፤ እሳትም በፊቱ ይነዳል» ሲል ቅዱስ ዳዊት ተናግሮአል (መዝ.፵፱(፶)፥፪-፫)፡፡

፪ኛ. ነቢዩ ኢሳያይስ «እነሆ እግዚአብሔር መዓቱን በቁጣ፤ ዘለፋውንም በእሳት ነበልባል ይመልስ ዘንድ ከእሳት ጋር ይመጣል» ሲል አረጋግጦአል (ኢሳ.፷፮፥፲፭)፤

፫ኛ. ነብዩ ዘካርያስ፤ «አምላኬ እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ይመጣል፡፡ በዚያም ቀን

በረዶና ውርጭ እንጂ ብርሃን አይሆንም» ሲል ትንቢት ተናግሮአል (ዘካ.፲፬፡፮-፯)፤

፬ኛ. ራሱ ጌታችን በቅዱሳን መላእክቱ ታጅቦ በታላቅ ክብር እንደሚመለስ ሲያረጋግጥ፤ «የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ይከፍለዋል» ብሎአል (ማቴ.፲፮፡፳፯)፤

በሌላ ክፍል «የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ከቅዱሳን ከመላእክቱ ጋር በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ በዚያን ጊዜ በክብሩ መንበር ይቀመጣል» ሲል ተናግሮአል (ማቴ.፳፭፡፴፩)፤

፭ኛ. እንዲሁም ራሱ አምላካችን አስደናቂውን ራእይ በገለጸለት በጌዱስ ዮሐንስ አንደበት ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደሚመጣ አስቀድሞ ሲያስጠነቅቅ፣ «እንሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዩ ከእኔ ጋር ነው፡፡ አልፋና ኦሜጋ፣ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ብሎአል (ራእ.፳፪፤፲፪-፲፫)፡፡

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክንርና በምስጋና ወደ ሰማይ ካረገ (ከወጣ) በኋላ (መዝ.፵፮(፵፯)፡፬-፯)፡ እርሱ በወሰነው ቀን እንደገና በታላቅ ክብርና በብዙ ምሥጋና ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ተመልሶ እንደሚመጣ ቅዱስ መጽሐፍ ያረጋግጣል(ማቴ.፳፬፤ ማር.፲፫፣ሉቃ.፳፩)፡፡

## ጥያቄ፡-ታዲያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣው እንዴት ነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣውማ በታላቅ ግርማና በብዙ ክብር፣ በክበበ ትስብእት፣ በግርማ መለኮት ማለት በግርማ መንግሥቱ በሰማይ ደመና ነው (ማቴ.፳፬፡፴)።

## ጥያቄ፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክበበ ትስብእት፣ በግርማ መለኮት ሲመጣ የሚመለሰው በስውር ነው ወይስ በግልጽ?

ጌታችን በግልጽና በታላቅ ግርማ ይመጣል ይኸውም እርሱ ራሱ እንዳለው፣ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደዚሁ በታላቅ ግርማ በቅዱሳን መላእክቱና በመባርቅት ታጅቦ ከሰማይ ወደዚህ ዓለም በግልጥ ይመጣል (ማቴ.፳፬፡፳፯)፡፡ በዚያን ጊዜ የምድር ወገኖች (የሰው ልጆች በሙሉ) ዋይ፣ዋይ ይላሉ፤ «የሰው ልጅም ማለት ክርስቶስም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል»(ማቴ.፳፬፡፴-፴፪)

ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ፣ «ናሁ ይመጽእ በደመና ሰማይ ወትሬእዮ ኵላ ወእልክቱሂ እለ ወግእዎ፣ ወይበክዩ በእንቲአሁ ኵሎሙ አሕዛብ ምድር» በብሎአል፡፡ ይኸውም «እነሆ በደመና ይመጣል፣ የሰው ዓይን ሁሉ ታየዋለች፣ የወጉትም ያዩታል፣ እርሱን ከማየት የተነሣ የምድር አሕዛብ ሁሉ ያለቅሳሉ» ማለት ነው (ራእ.፩፡፯-፰)፡፡

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ አስቀድሞ የሚታዩ ምልክቶች ምንና ምን ናቸው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ አስቀድሞ በዓለም ላይ የሚታዩ የጌታ የመምጣቱ ምልክቶች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ የሚከከተሉት ናቸው፡-

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረው መሠረት፡-

፩ኛ. ብዙ ሐሰተኞች ፣ «እኔ ክርስቶስ ነኝ» እያሉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይመጣሉ፤ እነርሱም ብዙዎችን ያስታሉ፤

፪ኛ. በየቦታው የጦርነት ወሬ ይሰማል፤ በየስፍራው ጦርነት ይሆናል፤

፫ኛ. ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፤

፬ኛ. ራብ ቸነፈርና የምድር መናወጥ (መንቀጥቀጥ) በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤

፭ኛ. ብዙ ክርስቲያኖች በእምነት ይሰናከላሉ፣ እርስ በርሳቸው አሳልፈው ይሰጣጣሉ፣

፮ኛ. ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፤ ብዙዎችን ያስታሉ፤

፯ኛ. ከዐመፅ ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች (ማቴ. ፳፬፥፮-፴፭፤ ማር.፲፫፥፫-፳፯ ሉቃ.፳፩፥፭-፴፮)፤

እነዚህና እነዚህን የመሰሉት ሁሉ የጌታችን መምጣት ምልክቶችና የመከራው መጀመሪያዎች ናቸው (ማቴ. ፳፬፥፰)፡፡ በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ያለሆነ ከዚህም በኋላ የመይሆን ታላቅ መከራ ይሆናል (ማቴ. ፳፬፥፳፩፤ ማር.፲፫፥፲፱)

## ጥያቄ፡-ጌታችን ለእውነተኞቹ ተከታዮቹ የሰጣቸው መመሪያዎች ምንና ምን ናቸው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለመላው ተከታዮቹ የሰጣቸው መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ኛ. እስከ መጨረሻው የሚጸና እሱ ይድናል (ማቴ. ፳፬፥፲፫)፤

፪ኛ. «በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ በዚህ ወይም በዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉ፤ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳን ለማሳት እስኪችሉ ድረስ ታላላቅ ምልክቶችንና አስደናቂ ሥራዎችን ያሳያሉ፤

፫ኛ. «እንሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ፤ እንግዲህ እንሆ ክርስቶስ በበረሃ ነው ቢሉአችሁ አትውጡ፤ እነሆ በእለፍኝ ነው ቢሉአችሁ አትመኑ፤ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ (የክርስቶስ) መምጣትም እንዲሁ ይሆናል» (ማቴ.፳፬፥፳፫-፳፰)፤

«ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠለዋም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ በደጅ እንደቀረበ እወቁ፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም፡፡ ሰማይና ምድር ያልፉል ቃሌ ግን አያልፍም» (ማቴ.፳፬፥፴፪-፴፭)፤ ሲል አስረድቶአቸዋል፡፡

## ጥያቄ፡-የጌታችን መምጣት እጅግ እንደ ቀረበ የሚያሳዩ ምልክቶች ምንና ምን ናቸው?

የጌታችን መምጣት እጅግ እንደ ቀረበ የሚያሳዩ (የሚጠቁሙ) ምልክቶች፡-

፩ኛ. ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ የክርስቶስ የመንግሥቱ ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል (ማቴ.፳፬፥፲፬ ማር፲፫፥፲.)፤

፪ኛ. «ከዚያ ሁሉ መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል ጨረቃ ብርሃንዷን አትሰጥም፤ ከዋክብት ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉ፤ በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ምልክት በሰማይ ይታያል» (ማቴ.፳፬፥፳፱)፤

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን የሚመጣበት ሰዓት ምን ጊዜ ነው?

ጌታችን መድኃኒታችን ተመልሶ የሚመጣበት ሰዓት አይታወቅም፤ ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደተገለጸው መምጣቱን የሚያመለክቱ ልዩ ልዩ ምልክቶችን ማወቅና ማየት የሚቻል መሆኑ ቢታወቅም ጌታችን የሚመጣበትን ትክክለኛውን ሰዓት ማወቅ የሚችል ፍጡር የለም (ማቴ.፳፬፥፴፮)፤

ስለዚሁ ራሱ ጌታችን የተናገረውን እንመልከት፤«ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአብ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፤ ወልድም ቢሆን የሚያውቅ የለም፡፡ በኖኅ ዘመን እንደ ነበር የሰው ልጅም መምጣት እንዲሁ ይሆናል፤ በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሲበሉና ሲጠጡ፣ ሲያጋቡና ሲጋቡ እንደ ነበሩ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፤ የሰው ልጅ (የክርስቶስ) መምጣትም እንዲሁ ይሆናል (ማቴ.፳፬፥፴፯-፴፱)፤

ጌታችን የሚመጣበት ትክክለኛው ቀንና ሰዓት በፍጡራን አእምሮ ሊታወቅ የማይቻል በመሆኑ፣ ራሱ ጌታችን ሁሉን በማስጠንቀቅ «ጌታችሁ በምን ሰዓት እንደሚመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ» ሲል ተናግሮአል (ማቴ.፳፬፥፵፪)፤ ቀጥሎም «ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ» ሲል አስጠንቅቆአል (ማቴ.፳፭፥፲፫)፤

በተጨማሪም ራሱ የሚመጣበትን ሰዓት ከራሱ በስተቀር ማንም ፍጡር ሊያውቅ ስለማይችል ሁሉም ነቅቶና ተግቶ መጠባበቅ እንደሚገባው እንዲህ ሲል አስጠንቅቆአል፤ «ጊዜው መቼ እንዲሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፤ ጸልዩም፡፡ ቤቱን ትቶ ወደ ሌላ አገር እንደ ሄደ ሰው ነው፤ ላገልጋዮቹም ሥልጣንና ለእያንዳንዱም ሥራውን ሰጥቶ በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ፡፡ እንግዲህ ማታም ቢሆን ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም በዶሮ ጩኸት ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ትጉ፡፡ ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉም ትጉ እላለሁ» (ማር፲፫፥፴፫-፴፯.)፤

«ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፣ ያ ቀን በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደ ወጥመድ ይደርስባቸዋልና፡፡ እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰው ልጅም (በክርስቶስ) ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁሉ ጊዜ ትጉ» ብሎ ጌታችን በጥብቅ አስጠንቅቆአል (ሉቃ.፳፩፥፴፬-፴፮)፡፨

## <u>ጥያቄ፡-</u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣው ለምንድር ነው?

ጌታችን ለእያንዳንዱ ሰው ዋጋውን እንደ ሥራው ለመክፈል ተመልሶ ይመጣል፡፡ ስለዚሁም ራሱ ጌታችን የተናገረውን እንመልከት፤ «የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉም እንደ ሥራው ያስረክበዋል» (ማቴ.፲፮፥፳፯) እንደገናም አስደናቂ ራዕይን በገለጸለት በቅዱስ ዮሐንስ አንደበት የሚመጣበትን ዓላማ ሲያስረዳ፤ «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡ አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው፤መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ሲል ተናግሮአል (ራእ.፳፪፥፲፪-፲፬)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለእያንዳንዱ ዋጋውን እንደ ሥራው ይከፍል ዘንድ ተመልሶ እንደሚመጣ ለማስረዳት እንደሚከተለው ጽፎአል፤ «እርሱ (ጌታ) ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ በበጎ ሥራ በመጽናትና ምስጋናንና ክብርን፤ የሚይጠፋውንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤ ለዓመፃ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙና ባድመኞች ለይ ግን ቁጣና መቅሰፍት ይሆንባቸዋል» (ሮሜ.፪፥፮-፰)፡፡ በሌላ ክፍል ስለዚሁ ሲያስረዳ፤ «መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ ለእያንዳንዱ በሥጋው (በሕይወተ ሥጋ ሳለ) የሥራውን ብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት ልንቆም ይገባናል» ብሎአል (፪ቆሮ.፭-፲)፡፡

## <u>ጥያቄ</u>፡-ጌታችን ፍጡር በማያውቀው ሰዓት በድንገት በታላቅ ግርማ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ ሰማያትና ምድር ምን ይሆናሉ?

ሰማያትና ምድር ያልፋሉ (ማቴ.፳፬፥፴፭)፤ ሰማያትና ምድር እንደሚያልፉ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የጌታችንን ቃል ተከትሎ እንዲህ ሲል ጽፎአል«የጌታችን ቀን ግን እንደ ሌባ (ባልታወቀ ሰዓት) ይመጣል በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤ የሰማይ ክብር በትልቅ ተኩሳት ይቀልጣልና ምድርና በምድር ላይ ያለው ሁሉ ይቃጠላል» (፪ጴጥ.፫፥፲)፡፡

ከዚያም በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚመጡ፤ (እንደሚገለጡ) ይህ ቅዱስ ሐዋርያ እንዲህ ሲል ጽፎአል «ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ፤ የእግዚአብሔር ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እየቸኮላችሁ (እየተጋችሁ) በተቀደሰ ኑሮ  እግዚአብሔርንም በመምሰል (በመልካም ስራ በመምሰል) ልትኖሩ ይገባችታል። ስለዚያ ቀንስ ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ክብር (ኃይል በትልቅ ትኩሳት ይፈታል። ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን» (2ኛጴጥ 3፥12-14) እንደዚሁም (ራእ 21፥1-3) ይመልከቱ።

## ጥያቄ፦ «የጌታ ቀን እንደሌባ ሆኖ ይመጣል» ያለው ምን ማለት ነው?

ሌባ ባለቤት ባላሰበበትና ባልተጠበቀበት ሰዓት እንደሚመጣ ሁሉ የጌታችንም አመጣጥ እንደዚሁ በድንገት የሚሆን መሆኑን ለማመልከት ነው። ስለዚህ ራሱ ጌታ ሲናገር «ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንደሚመጣ ቢያውቅ ኖሮ በነቃ፣ ቤቱንም እንዲቆፈር ባልተወም ነበር። ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፣የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣል» ብሎአል (ማቴ 24፥44-45)

# <u>የሰው ልጆች ትንሣኤ</u>

«ሙታን ሕያዋን ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሳሉ» ኢሳ. 26፥19

## <u>ጥያቄ</u>፦ ሰው ሞቶ ከተቀበረ፤ ሥጋው ወደ አፈር ከተመለሰ፣ ከፈረሰና ከበሰበሰ በኃላ እንደገና ሕይወት አግኝቶ መነሳት ይችላልን?

አዎን ይችላል። በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰው ሁሉ ከሞተና ከተቀበረ በኃላ እንደገና በእግዚአብሔር ኃይል ሕይወትን አግኝቶ ሕያው ሆኖ ይነሳል። በአዳም በደል ምክንያት በአዳምና በአዳም ልጆች ላይ ሁሉ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» ብሎ እግዚአብሔር ሞት ስለፈረደባቸው(ዘፍ. 3፥19) ሁሉም ለመሞት በቁ፣ ወደ መቃብርም ወርደው ወደ አፈር ተመለሱ። ነገርግን በዓለም መጨረሻ እንደገና የሞቱተት ሰዎች በሙሉ በእግዚአብሔር ታይል ከሞትና ከመቃብር ይነሳሉ። «ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁም ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ» ተብሎ ተጽፎአልና።(1ኛ ቆሮ.15፥22)

## <u>ጥያቄ</u>፦ የሰው ልጆች ትንሣኤ በስንት ይከፈላል?

የሰው ልጆች ትንሣኤ በሦስት ይከፈላል።
ይኸውም፦

1. የመንፈስ ትንሣኤ (በመንፈስ መነሳት)
2. የነፍስ ትንሣኤ (በነፍስ ብቻ መነሳት)
3. የሥጋና የነፍስ ትንሣኤ (የመጨረሻው ትንሣኤ) ነው።

## <u>ጥያቄ</u>፦ የመንፈስ ትንሣኤ እንዴት ነው?

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ከኃጢአት፥ ከጨለማ፥ ከሞት ይነሳሉ፣ የሕይወትን ብርሃን ያገኛሉ(ዮሐ. 8፥12)። ጌታችንን ያላመኑና እርሱን ያልተከተሉ ሁሉ ሙታን (ሙታነ መንፍስ) እንደሚባሉ (ማቴ. 8፥22፥ ሉቃ.9፥59-60) በሕይወተ ሥጋ ያሉ፣ በጌታችን ያመኑ በመንፈ

ስ ሕያዋን ይባላሉ፣ በመንፈስም ይመላለሳሉ። ይህንን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖችበላከው መልእክቱ ሲጽፍ «እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን፣ ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው።» ብሎአል። ሮሜ. 8፥9-16። በዚሁ መልእክቱ በሌላው ክፍል «እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደሞታችሁ፣ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ» ሲል አስተምሮአል (ሮሜ 6፥11)

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲጠመቁ ክርስቶስን በሞቱ እንደሚመስሉት ተጠምቀው ከውኃው ሲወጡ ደግሞ ክርስቶስን በትንሣኤው ይመስሉታል። በእምነትና በጥምቀት አንድ የሆኑ ሁሉ በትንሣኤው ክርስቶስን ስለሚመስሉ፣ በመንፈሳዊ ትንሣኤ የሚገኙ ሁሉ ሕያዋን ይባላሉ።ይህንን ምስጢር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሚከተለው አገላለጽ ጽፎታል «ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደፊት እንዴት አድርገን በእርሱ(በኃጢአት) እንኖራለን? ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ፤ እንዲሁም እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውንም በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር አንድ እንሆናለን።» (ሮሜ 6፥2-5)

ከዚህ በላይ አጠር ባለ ሁኔታ የተገለጸው የመንፈስ ትንሣኤ በቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሰፋ ያለ ሐተታ ተሰጥቶበታል። ሊቃውንቱ መንፈሳዊውን ትንሣኤ፣ «ትንሣኤ ልቡና» ብለውታል። ይኸውም በዮሐንስ ራእይ 20፥1-7 ያለውን ንባብ ሲተረጉሙ «እሙንቱስ የሀይው፣ ወይነግሡ ምስለ ክርስቶስ አሥርተ ምዕተ ዓመተ፣ወባእዳንስ ሙታን ኢይትነስኡ፣ እስከ አመ ይትፌጸም ዝንቱ አስርቱ ምእት ዓመት»፣ « እነርሱ ትንሣኤ ልቡና ይነሳሉ፣ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዘመን ይነግሣሉ (ይህ ዘመን ሥጋዌን፣ ዘመነ ሐዲስን ይመለከታል።)» ሌሎቹ «ሙታን ግን ሺህ ዓመት (ዘመነ ሥጋዌ) እስኪፈጸም ድረስ አይነሱም እያሉ ያትቱታል (ራእ 20፥1-8 እንድምታውን ይመልከቱ)

## <u>ጥያቄ፦</u> የነፍስ ትንሣኤ ማለት እንዴት ነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሐደው ሥጋ ስለ እኛ መከራ መስቀልን ተቀብሎና በለበሰው ሥጋ ሞትን ቀምሶ በሰው ልጆች መካከል የነበረውን ጥል በመስቀሉ ገድሎ ለሰው ልጆች በሙሉ አንድ የመሆንን ሥልጣን ሰጠ (ኤፌ.2፥16)። በሰው ልጆች ላይ የተጻፈውን የዕዳ (በደል) ደብዳቤ ደምስሶና በመስቀልም የሰይጣንን አለቅነትና ስልጣን ገፍፎ ድል በመንሳት (ቆላ 2፥14-15) በወኅኒ(በሲኦል) ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው(1ኛጴጥ 3፥19) ማለት ነፃነትን ሰበከላቸው፣ ከሲኦል አወጣቸው ስለዚህ ይህ የነፍስ ትንሣኤ ወይም «ትንሣኤ ነፍሳት» ይባላል።
ቀደም ብሎም በነቢዩ በኢሳያስ እንደበት ነፍሳት ከሲኦል እንደሚወጡ (እንደሚነሱ)ትንቢት ተበግሮ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል፣ «እለ ውስተ ሲኦል ጣሁ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሰቱ ወርእዩ ብርሃነ አቢየ» «በሲያል ያላችሁ ውጡ በጨለማ ውስጥ የተቀመጣችሁ ውጡ፣ ታላቁንም ብርሃን እዩ» ተብሎ ትንቢት ተነግሮ ነበር(ኢሳ 49፥9 በግእዙ)። በትንቢቱ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በሥጋው በመስቀል ተሰቅሎና ሞትን ቀምሶ በአካለ ነፍስ(በነፍሱ) ወደሲያል ወርዶ በሰይጣን ተይዘው የነበሩትን ነፍሳት ነፃ አወጣ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ሲያልን አሸንፎ በሲያል ታስረው የነበሩትን ነፍሳት ነፃ ማውጣቱን የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በየድርሳናቸውአረጋግጠዋል።
ኤልመስጦአግያ በተባለው የሃይማኖተ አበው ክፍል አበው ቅዱሳን «ሰው ሆኖ መከራን ከተቀበለ በኃላ ወደ ሲኦል ወርዶ የሙታንን ነፍሳት የማረከ (ነፃ ያወጣ) እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው። በሲያል የነበሩትን ነፍሳት በልዕልና ወዳለች ወደ ገነት ያወጣቸው ከክብራቸው ወጥተው የነበሩትን ወደ ቀደመ ክብራቸው የመለሳቸው እርሱ ክርስቶስ ነው።» ሲሉ መስክረዋል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ 32 ቁ. 20) ረድእ ሐዋርያት (የሐዋርያት ተከታይ) የነበረው ቀሬኔዎስ(ኢሬሜዋስ) ደግሞ ስለዚሁ ምስጢር ሲመሰክር «ለሥጋ በሚስማማ ሕማም ታመመ፤ ተሰቀለ፣ በእግዚ

አብሔርነቱ ኃይል ከሙታን ተለይቶ ተነሳ፣ ይኸውም መለኮቱ ነው።ወደ ሲኦልም ወርዶ ነፍሳትን ማረከ»ሲል አስረድቶአል።(ሃይማኖተ አበው ገጽ32 ቁ. 20)

ሐዋርያዊ ቅዱስ አትናቴዎስ ዘእስክንድርያም ከላይ የተገለጸውን ትምህርት ተከትሎ «ስለ ፍጥረት ሁሉ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ሥጋው በመስቀል እንዳለ ነፍሱ ግን ወደ ሲኦል ወርዳ በዚያ ተግዘው የነበሩትን ነፍሳት አዳነች፣ ሲያልንም ማረከች (በዘበዘች)፣ ፍጥረትንም ሁሉ ገንዘብ አደረገች።» ብሎአል። ቀጥሎም ይህንኑ ሲያብራራ «ወሥጋሁ አንበአ ሙታነ እለ ሀለው ውስተ መቃብር፣ ወነፍሱሂ ወረደት ውስተ ሲኦል፣ ወፈትሀት ነፍሳተ እንተ ሙቅህቶን ይነብራ ውስተ ሲኦል»፣ «ሥጋው በመቃብር የነበሩትን ሙታን አስነሳ፣ ነፍሱም ወደ ሲኦል ወርዳ በሲኦል ታስረው የነበሩትን ሙታን ፈታች (ነጻ አወጣች) ብሎአል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ 81 ቁ.20) በሌላ ክፍልም ይህ ቅዱስ አባት እንዲህ ብሏል። «ውእቱ ቃል ዘይትዋሃድ ምስለ ሥጋ ወነፍስ፣ ውእቱ ወረደ በነፍስተ ሥጋ ውስተ ሲኦል ወሰበከ ግእዛነ ለነፍሳት»፣ «ከነፍስና ከሥጋ ጋር የተዋሐደው ቃል ነው። እርሱ የሥጋ ሕይወት በምትሆን በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ለነፍሳት ነጻነትን ሰበከ» ሲል አስረድቶአል።(ሃይማኖተ አበውገጽ98 ቁ. 33)

ታላቁ አባት ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም ስለዚሁ ሲያስተምር «ወካእበ ወረደ ውስተ መካናት እንተ መትህተ ምድር ወአግአዘ ነፍሳተ እለ ሀለዋ ህየ ወጼወወ ሲኦለ በመለኮቱ» «ዳግመኛ በዚያ በሲኦል ተግዘው የነበሩትን ያድን ዘንድ ወደ ሲኦል ወረደ። በዚያ የነበሩትን ነፍሳት ነፃ አወጣ፣ በመለኮቱም ሲኦልን በረበራት» ብሎአል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ 258 ቁ. 30)። ስለዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲኦልን በርብሮ፣ በዚያ የነበሩትን ነፍሳት ስለአዳነ ና ነፃም ስላወጣ መዳኑና ነፃ መውጣቱ የነፍሳት ትንሣኤ (የነፍስ ትንሣኤ ይባላል። የነፍስ ትንሣኤ ደግሞ መደምደሚያው ወይም መፈጸሚያው የመጨረሻ ትንሣኤ ነው። እርሱም የሥጋና የነፍስ ትንሣኤ ነው።

## ጥያቄ፡- የሥጋና የነፍስ ትንሣኤ የሚባለው እንዴት ነው?

በዓለም ፍጻሜ መጨረሻ ላይ ጌታችን በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ሲመጣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ የሞቱ ሰዎች በሙሉ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተዋሕዳ ይነሳሉ። ይኸውም የሥጋና የነፍስ ትንሣኤ ይባላል። ሊቃውንትም ትንሣኤ ዘጉባኤ ይሉታል። የሰው ዘር ሁሉ ትንሣኤ ማለት ነው። (ዮሐ. 5፣29)

## ጥያቄ፡-ሰው ሞቶና ተቀብሮ አካሉ ከፈረሰና ከበሰበሰ በኃላ እንደገና እንዴት ሊነሳ ይችላል?

ሰው ጥንቱንም ቢሆን ሥጋዊ አካሉ የተፈጠረው ከመሬት (ከአፈር) ነበር። ቅዱስ መጽሐፍም እንደሚመሰክረው «እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከምድር አፈር አበጀው (ሠራው) በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት። በዚህ ጊዜ ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።» (ዘፍ. 2፣7)። ስለዚህ በእግዚአብሔር ጥበብ ከአፈርና ከሕያዊት ነፍስ ተዋሕዶ የተፈጠረው ሰው ወድቶና ፈቅዶ በአደረገው ኃጢአት «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» ተብሎ ሞት ተፈረደበት። በሞተ ሥጋም ሞተ ነፍስ ታዘዘበት (ዘፍ 3፣19-20)። በዚህም ምክንያት ሰው በልዩ ልዩ ምክንያት ሥጋውና ነፍሱ ሲለያዩ በተፈረደበት መሠረት ሥጋው ወደ መጣበት ወደ መሬት ይመለሳል (ይቀበራል)። ነፍሱም ፍርዳን ለመቀበል ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች። (መክ 12፣7)። ጊዜው ሲደርስ (ዓለም ሲፈጸምም) እንደገና በእግዚአብሔር ኃይል ሰው ሥጋውና ነፍሱ ተዋሕደውለት ከሞት ከመቃብር ይነሳል።

## ጥያቄ፡- ሙታን (የሞቱ ሰዎች) እንደሚነሡ በመጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ የተነገረ ትንቢት አለ?

አዎን አለ። መጽሐፍ ቅዱስ ሙታን እንደሚነሱ በብዙ ቦታ ያረጋግጣል። ሙታን እንደሚነሱ ከሚያረጋግጡት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል ለአስረጂነት ይሆኑ ዘንድ ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመልከት።

1. ቅዱስ ዳዊት ሰዎች እንደሚሞቱና እንደገናም እንደሚነሱ ሲናገር «ፊትህን ስትመልስ(ስትሰ ውር) ይደነግጣሉ፣ ነፍሳቸውን ታወጣለህ፣ ይሞታሉም ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም» ብሎአል መዝ 103(104 29-30)

2. ነቢዩ ኢሳያስም «ሙታንሰ ይትነስኡ፣ ወየሀይው እለ ውስተ መቃብር ወይትፌስሁ እለ ውስ ተ ምድር እስመ ጠል ዘእምታቤከ ሕይወቶሙ ውእቱ» «አንተ ከምትሰጣቸው የሕይወት ጠል የተነሳ ሙታን ይነሳሉ። ከመቃብር ያሉት ሁሉ ይድናሉ (ሕይወት ያገኛሉ) በምድርም ያሉት ደ ስ ይሰኛሉ»ብሎአል ኢሳ. 26፥18-19 ግእዙን ይመልከቱ) በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ « ሙታን ሕያዋን ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሳሉ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወ ጣለች» ተብሎ ተመዝግቦአል።

3. ነቢዩ ዳንኤልም ሙታን እንደሚነሱ ሲመሰክር «በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆም ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሳል። በህዝቡ ላይም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል። በዚያ ዘመን በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ የተገኘ ሕዝብ እያንዳንዱ ይድናል። በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዋች ይነቃሉ እኩሌቶቹ ወደ ዘላ ለም ሕይወት፣ እኩሌቶች ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ይሄዳሉ» ብሎአል። (ዳን 12፥1-3)

4. በነብዩ በሆሴኤ መጽሐፍ ደግሞ «ወያሀይወነ በሰኑይ መዋእል ወአመ ሳልስት እለት ንትነሳእ ወነሀዩ በቅድሜሁ» «ከሁለት ቀን በሁዋላ ያድነናል በሶስተኛውም ቀን እንነሳለን በፊቱም በህ ይወት እንኖራለን።» ተብሎ ተጽፎአል። (ሆሴ 6፥2)

5. እራሱ ጌታችንም ሙታን እንደሚነሱ ሲያረጋግጥ «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምጹን (የጌታን ድምጽ) የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል። መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፋም ያደረጉ ለ ፍርድ (ለኩነኔ) ትንሣኤ ይወጣሉ» ብሎአል።(ዮሀ 5፥9)

ይህ አምላካዊ ቃል ሁለት ዓይነት ትንሣኤ እንዳለ ያመለክታል። ይኸውም፦

ሀ. የሕይወት (የድኅነት) ትንሣኤ

ለ. የሐሳር (የመከራ) ትንሣኤ ነው።

መልካም የሠሩ መልካም ስራቸውን ይዘው ይነሱና ወደ ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚሄዱ መጥፎ ሥራ የሠሩ ደግሞ ክፉ ሥራቸውን ተሸክመው ይነሱና ወደ ዘላለማዊ ቅጣት እንደሚላኩ የሚ ያመለክት ቃል ነው።

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ቀን (ዓለም ሲፈጸም) ሙታንን እንደሚያስነሳ ብዙ ጊዜ ተናግሮአል። «አብ ከሰጠኝም ሁሉ አንድ ስንኳ እንዳላጠፋ ነገር ግን በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድም ይህ ነውና» ብሎአል (ዮሐ 6፥39) እንደዚሁም «ወ አልቦ ዘይክል መጸአ ታቤየ፣ እመ ኢሰሀቦ አብ ዘፈነወኒ ወአነ አንስኦ በድታሪት እለት» «የላከ ኝ አብ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም እኔም በመጨረሻው ቀን አስነ ሳዋለሁ» ሲል ተናግሮአል። (ዮሐ 6፥44) ቀጥሎም «ሥጋዩን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ» ብሎአል።(ዮሐ 6፥54)

7. በዘመነ ብሉይ የነበረው ነቢዩ ዕዝራም በምድር የተቀበሩ ሬሳዎችና በሲኦል የሚገኙ ነፍሳት እንደሚነሱ ሲመሰክር «መዋቲ (ሟች) የሚኖርበት ዓለም ያልፋል፣ምድርም በውስጡዋ ያሉትን (የተቀበሩትን) ትሰጣለች፣ መሬትም በውስጡ ያሉትን ይሰጣል። ባህርም፣ ሲኦልና ገነትም በው ስጣቸው ያሉትን ነፍሳት ይሰጣሉ» ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር (ዕዝ ሱቱ 5፥31-33)።

## <u>ጥያቄ፦</u> ሙታን የሚነሱት እንዴት ነው?

ሙታን እንዴት እንደሚነሱ ቅዱስ መጽሐፍ የሚለውን እንመልከት፦

«እስመ ይኤዝዝዘ እግዚእነ ምስለ ቃለ ሊቀ መላእክት ወንፍሀተ ቀርን ዘእግዚአብሔር ዘይወር
ድ እምሰማይ፣ ወይትነሥኡ ምውታን መቅድመ እለ ሞቱ በሃይማኖተ ክርስቶስ» ይላል። ይኸ
ውም «ራሱ ጌታ ያዛል። በመላእክት አለቃና በመለከት ድምጽ ከሰማይ ይወርዳል፣ በክርስቶስ
አምነው የሞቱት አስቀድመው ይነሳሉ» ማለት ነው። (1ኛ ተሰ.4፥16)
ቅዱስ ያዕቆብ ኤጲስ ቆጶስ ዘሥሩግም ከዚህ በላይ ያለውን ቃል መሠረት አድርጎ ሙታን እን
ዴት እንደሚነሱ ከዚህ እንደሚከተለው ጽፎአል። «ሶስት ጊዜ መለከት ይነፋል ይኸውም ሙ
ታንን የሚያነቃ ነው/ በመጀመሪያው አዋጅ በዓለም ዳርቻ የተበተነ ሥጋ (የሰው ሥጋ) ትቢያ
የሆነ ሁሉ ይሰበሰባል። በላይ ያለውና በታችም ያለው፤ በባህር ያለውና በየብስም ያለው፣ በአ
ራዊትም ሆድ የነበረው፤ በልዩ ልዩምክንያት የሞተው ፈጽሞ ያረጀውና የጠፋው፣ በምድር ላይ
የወደቀው የሥጋ ቅርፊትም ሁሉ ወደ ቀድሞ መገኛው ይሰበሰባል። በሁለተኛው አዋጅ አጥንቶ
ች ከሥጋ ጋር ይያያዛሉ፣ ያለመንቀሳቀስና ያለመናወጥም እስከ ጊዜው ድረስ ፍጹም በድን ይ
ሆናሉ። በሶስተኛው አዋጅ ሙታን እንደ ላይን ጥቅሻ (ከመቀጽበት) ይነሳሉ ጻድቃንና ኃጥአን
ክፉም ቢሆን በጎም ቢሆን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሠሩትን ከምድር የተከተላቸውን ሥራቸ
ውን ተሸክመው ይነሳሉ ጻድቃንን በቀኝህ ኃጥአንንም በግራህ ታቆማለህ» ሲል ጽፎአል (ቅዳሴ
ዘያዕቆብ ዘሥሩግ ቁ. 89-92)

## <u>ጥያቄ፦</u> ጌታችን ዳግም ሲመጣ የቅዱሳን መላእክት ሥራ (ተልዕኮ) ወይም ያገል ግሎት ድርሻቸው ምንድን ነው?

ጌታችን ዳግም ሲመጣ የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት ምን እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ
አልና ቀጥለን እንመልከት። ጌታችን ስለ ቅዱሳን መላእክት አገልግሎት ሲያስረዳ «የሰው ልጅ
(ክርስቶስ) መላእክቱን ይልካል። ከመንግሥቱም እንቅፋትን፣ ዐመፃንም የሚያደርጉትን ሁሉ ይ
ለቅማሉ፤ ወደ እቶን እሳትም ይጥላቸዋል። በዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨትም ይሆናል»ብሎአ
ል (ማቴ13፥41-43)። ቀጥሎም ያን ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ምን እንደሚሠሩ ሲያመለክት«በዚያ
ን ጊዜ የሰው ልጅ(ክርስቶስ) ምልክት በሰማይ ይታያል፣ በዚያን ጊዜ የምድር ወገኖች ሁሉ ዋ
ይ ዋይ ይላሉ የሰውንም ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል። መላእክ
ቱንም ከታላቅ የመለከት ድምጽ ጋር ይልካቸዋል። ከሰማያት ዳርቻው አስከ ዳርቻው፣ ከአራ
ቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ» በማለት አስረድቶአል (ማቴ 24፥30-32፣ ማር 13
፥26-29)። ስለዚህ በዕለተ ምጽአት የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት ምን እንደሆነ ከዚህ በላይ
በአጭሩ ተገልጦአል።

## <u>ጥያቄ፦</u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ወደዚህ ዓለም በሚመጣበ ት ጊዜ በጌታችን ኃይል የሚነሱ ሙታን ወዴት ይሄዳሉ?

እንደየሥራቸው ፍርዳቸውን ለመቀበል በጌታችን ቀኝና ግራ ይሰበሰባሉ። ስለዚሁም ራሱ ጌታ
ችን የተናገረውን እንመልከት።
«የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ (በሚ
መጡበት) ጊዜ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን (በመንበረ ክብሩ) ይመጣል። አሕዛቡም ሁሉ በፊቱ
ይሰበሰባሉ። እረኛ በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርሱም እንዲሁ ይለያቸዋል። በጎቹን በቀኙ፣
ፍየሎቹን በግራው ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ ያባቴ ብ
ሩካን ኑ ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፣ ተርቤ አብልታች
ሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሁኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛል
ና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና። ጻድቃንም መልሰ
ው እንዲህ ይሉታል፦ ጌታ ሆይ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ? ወይስ ተጠምተህ አይተንህ መ
ቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?ወ
ይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወዳንተ መጥተን ጠየቅንህ? ይሉታል። ንጉሡም መልሶ

እውነት እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።

በዚያን ጊዜም በግራው ያሉትን ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን! ለሰይጣንና ለመላእ ክቱ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ፣ ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ተጠምቼ አላጠጣችሁኝ ምና፣ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየ ቃችሁኝምና። እነርሱ ደግመው ይመልሱና ጌታ ሆይ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል። ያን ጊዜ እውነት እውነት እላችኋለው ከሁሉ ለሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁ ለእኔ ደግ ሞ አላደረጋችሁም ብሎ ይመልስላቸዋል። እነዛ ኃጥአን ወደ ዘላለም ቅጣት፣ ጻድቃን ግን ወ ደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ» (ማቴ 24፥31-46)

## <u>ጥያቄ፦</u>ጌታችን ዳግመኛ ሲመጣ ለሁሉም ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው እንደሚከፈለው ማለት ለኃጥአን እንደ ሥራቸው ለጻድቃንም እንደሥራቸው እንደሚከፈላቸ ው ከዚህ በላይ ተረጋግጣል። ከዚህ ሌላስ ስለዚሁ አስቀድሞ የተናገረው ነገ ርና ያስተማረው ትምህርት አለን?

አዎን አለ። «የሰው ልጅ (ክርስቶስ) ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል» ሲል ተናግሮአል። (ማቴ 16፥27) በሌላ ጊዜም አስገ ራሚ ራእዩን ለገለጸለት ለዮሐንስ ራሱ ጌታችን «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍለው ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ዘንድ አለ። አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው እ ኔ ነኝ» ሲል ነግሮታል (ራዕ 22፥12-14)

ቅዱስ ዮሐንስም በራዕዩ ሰማያትና ምድር እንደሚያልፉ የሞቱት ሰዎች በሙሉ እንደሚነሱና እንደየሥራቸው ዋጋቸውን ከጌታ እንደሚቀበሉ እንደሚከተለው ጽፎአል «ታላቅና ነጭ ዙፋን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም ።ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ። መጻሕፍትም ተከፈቱ (ተገ ለጡ) ሌላም መጽሐፍ ተገለጠ ፣ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው። ሙታንም በመጽሐፉ እን ደተጻፈው የሥራቸውን ብድራት ተከፈሉ። ባህር በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ። ሞትና ሲያልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለው ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ፣ ይህም ያእሳት ባህር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕ ይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ማንኛውም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣለ» (ራዕ 20፥11-15)

## <u>ጥያቄ፦</u> ጌታችን ዳግመኛ ሲመጣ ሙታን በሙሉ እንደሚነሱ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስም በብዙ ቦታ ያረጋግጣል ነገር ግን ሙታን የሚነሱት በምን ዓይነት አካል ነው?

ሙታን የሚነሱት በተሐድሶ ነው፣ ማለት በመንፈሳዊ አካል ነው። ሙታን በመንፈሳዊ (በረቂቅ) አካል እንደሚነሱ ራሱ ጌታችን ለሰዱቃዊያን በሰጠው መልስ አረጋግጡዋል። ሰዱቃውያን ጌ ታችንን ሊፈትኑት ፈልገው እንዲህ ሲሉ ጠየቁት «መምህር ሆይ ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወ ልድ ቢሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ (ወርሶ) ለወንድሙ ዘር ይተካለት አለ። ሰባት ወንድማ ማች በእኛ ዘንድ ነበሩ ፊተኛው ሚስት አግብቶ ሞተ ዘርም ስላልተወ ሚስቱን ወንድሙ አገባ ት እንዲሁም ሁለተኛው፣ ሶስተኛውም እስከ ሰባተኛው ድረስ (ሰባቱም ሁሉ) ከሁሉም በታላ ሴቲቱ ሞተች በትንሣኤ ቀን ከሰባቱ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች?» አሉት። ኢየሱስም «መጻሕ ፍትና የእግዚአብሔርን ቃል አታውቁምና ትስታላችሁ። በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእ ክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡም» ብሎ መለሰላቸው (ማቴ 22፥23-32) ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው ወንጌል ጌታችን ለሰዱቃውያን የሰጠው መልስ እንዲህ የሚልነው «የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ ይጋባሉ በወዲያኛው ዓለምና በትንሣኤ ሙታን የሚነሱ እነዚያ ግን አያገቡም አ ይጋቡም እንደ መላእክት ናቸውና።» አላቸው (ሉቃ 20፥34-36)

ሙታን ሁሉ ሕያዋን እንደሚሆኑ ማለት እንደሚነሱ ጌታችን ለሰዱቃውያን እንዲህ ሲል አስረ ድቶአቸዋል «ሙታን እንደሚነሱ ግን ለሙሴ ደግሞ በቁጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር አምላ ክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ (ነኝ) በማለቱ አስታወቀ፣ ሁሉ ለእርሱ ሕያዋን ስለሆ ኑ የሕያዋን (በትንሣኤ ሙታን ጊዜ የሚነሱ) አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም» (ሉቃ 20፥37-39፣ማቴ 22፥32-33

## ጥያቄ፦ ሙታን በተሐድሶ ማለትም በመንፈሳዊ (በረቂቅ) አካል እንደሚነሱ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው ትምህርት አለ?

አዎን አለ። ሙታን በመንፈሳዊ አካል እንደሚነሱ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፎአል« ነገ ር ግን ሙታን እንዴት ይነሳሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ዘር ካልሞተ (ካልተቀበረ) ሕያው አይሆንም፣ የምትዘራው ስንዴ ቢሆን ፣ ከሌላም ዓይነት የአንዱ ቢሆን ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይ ደለም። የሰው ሥጋ ግን አንድ ነው። የእንስሳም ሥጋ ሌላ ነው፣ የወፎችም ሥጋ ሌላ ነው፣ የአሣም ሥጋ ሌላ ነው። ደግሞም ሰማያዊ አካል አለ፣ ምድራዊ አካልም አለ፣ ነገር ግን የሰማ ያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፣ የምድራዊ አካል ክብርም ልዩ ነው፣ የፀሐይ ክብር ሌላ ነው በክ ብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ልዩ ነውና (ይበልጣልና) የሙታን ትንሣኤም እንዲሁ ነው።በ መበስበስ ይዘራል፤ ባለመበስበስ ይነሳል፣ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሳል። በድካም ይዘራ ል በኃይል ይነሳል። ፍጥረታዊ (ሥጋዊ) አካል ይዘራል መንፈሳዊ አካል ይነሳል። ፍጥረታዊ ( ሥጋዊ) አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ» (1ኛ.ቆሮ 15፥35-45)።

ፈራሽና በስባሽ የሆነው ሥጋ በትንሣኤ ጊዜ ታድሶ የማይፈርስና የማይበሰብስ ሆኖ እንደሚነሳ ይህ ቅዱስ ሐዋርያ እንዲህ ሲል ያስረዳል «የዚያን የመሬታዊ(አዳም) መልክ ደግሞ እንደ ለበ ስን፣ የሰማያዊውን(የክርስቶስን) መልክ ደግሞ እንለብሳለን። ነገር ግን ወንድሞቼ ሆይ ይህንን እላለሁ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ አይችልምና የሚበሰብሰው የማይበሰብ ሰውን አይወርስም።እነሆ አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ ሁላችንም እናንቀላፋለን ነገር ግን የታ ለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችንም በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን። መለከት ይነፋልና ሙ ታንም የማይበሰብሱ ሆነውይነሳሉ እኛም እንለወጣለን። ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊ ለብስ፤ ይህ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና፣ ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበ ሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመነሳት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል» (ሆሴ 13፥14፣ 1ኛቆቆሮ 15፥49-55)

## ጥያቄ፦ሙታን በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ማለት በዚህ ዓለም ሳሉ በሠሩት ሥራ እንደ ሥራ ቸው መጠን ፍርዳቸውን ከጌታ ከተቀበሉ በኃላ ወዴት ይሄዳሉ?

ጻድቃንና ኃጥአን እንደየሥራቸው መጠን ፍርዳቸውን ከተቀበሉ በኃላ ኃጥአን ወደ ዘላለም ቅ ጣት ሲሄዱ ጻድቃን ደግሞ ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ (ማቴ 25፥46)። ጌታችን አስቀድሞ እንደተናገረ «ኃጢአተኞች (ንስሐ ያልገቡት) በሙሉ ወደ እቶን እሳት ይጣላሉ። በዚያም ልቅ ሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት( በመንግሥተ ሰማያት ) እንደ ፀሐይ ያበራሉ።» (ማቴ.13፥42-43)። በሕይወተ ሥጋ ሳለ እግዚአብሔርን አምኖ መልካ ም ሥራን ሠርቶ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘ ማንኛውም ሰው ወደ እሳት ባሕር ይጣላ ል (ራእ 20፥15) «የሚፈሩ ማለትም ለማመን የፈሩ (የሚያፍሩ)፣ የማያምኑ፣ የርኩሳንም፣ የነፍ ስ ገዳዮችም፣ የሴሰኞችም፣ የአስማተኞችም፣ የጣዖት አምላኪዎችም፣ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕ ድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባህር (የእሳት ባሕር) መጣል ነው። ይኸውም ሁለተኛ ሞ ት ነው» ሲል ቅዱስ ዮሐንስ አስረድቶአል። (ራእ. 21፥8-9)

በነቢዩም እንደተነገረው የዓለም መጨረሻ በሚሆንበት በምጽአት ጊዜ በምድር ትቢያ ውስጥ ያ ንቀላፉት (ካንቀላፉት ብዙዎቹ) ይነቃሉ። እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ ሀፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና ይሄዳሉ። ጥበበኞች (ጻድቃን) ደግሞ እንደ ሰማይ ጸዳል ወደ ጽድቅ የሚመለሱ (ንስሐ የሚገቡ) ብዙ ሰዎችም እንደ ከዋክብት ይደምቃሉ (ዳን12፥-2-4) አገ ልጋዮቹም እግዚአብሔርን ያመልኩታል ፊቱንም ያያሉ ስሙም በግምባራቸው ይሆናል።«ከእን

ግዲህ በኃላ ሌሊት አይሆንም፣ እግዚአብሔር አምላክ በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና፣ የመብራ
ት ብርሃን የፀሐይም ብርሃን አያስፈልጋቸውም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ»(ራእ. 22፥4-5
)

**ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ**1991 **ካሳተሙት የተወሰደ።**